# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 302 የካቲት 14 2006 ገጽ 1

ወያኔና ስር የሰደደዉ ዘረኛ ስርዐቱ ከኢትዮጵያ ምድር ላይ እስካልተነቀሉ ድረስ ወያኔ ዝርፊያዉን የወያኔ መከላከያ ተቋምም የወያኔንና የደገፊዎቹን ዝርፊያ በመሳሪያ ማጀቡ አይቆምም። የወያኔን ዝርፊያ ለማስቆምና አገራችንን ከተጋረጠባት አሳሳቢ አደጋ ለመታደግ ብቸኛዉ መንገድ ወያኔን ከሥልጣን ማስወገድ ብቻ ነዉ። ግንቦት 7 የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የጀመረዉ ህዝባዊ ትግል እንደ አገር መከላያከያ አይነቶቹ ቁልፍ የአገር ተቋሞች በሚሰሯቸዉ ስራዎች ሁሉ የአገርንና የህዝብን ጥቅም እንዲያስጠብቁ ለማድረግ ነዉ።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን በራሱ አብራሪ ተጠልፎ ጀኔቭ ዉስጥ አረፈ

በኢትዮጵያ ባለቤትነት የተመዘገበና የበረራ ቁጥሩ 702 የሆነ የመንገደኞች አውሮፕላን ተጠልፎ ጀኔቭ ስዊዘርላንድ ማረፉን ዓለማቀፍ ሚዲያዎች በመቀባበል እንደዘገቡት ታወቀ። አብራሪዎቹንና የበረራ አስተናጋጆችን ጨምሮ ከ200 በላይ መንገደኞችን አሳፍሮ የነበረውና እሁድ እኩለ ሌሊት ላይ ከአዲስ አበባ ዓለማቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ተነስቶ በካርቱም ሱዳን አድርጎ ሮም ጣሊያን መድረስ የነበረበት ሲሆን ከአዲስ አበባ እንደተነሳ በረዳት አብራሪው ተጠልፎ ሁሉንም ትቶ አቆራርጦ ወደ ስዊዘርላንድ በመገስገስ ሰኞ ጠዋት ጀኔቭ ማረፉን ዘጋቢያችን ከስፍራው ገልጿል።

ጣሊያናዊ ዜግነት ያለው ዋና አብራሪ ወደ መታተቢያ ቤት መግባቱን እንደ አጋጣሚ የተጠቀመው ኢትዮጵያዊው ምክትል አብራሪ፤ የአብራሪዎቹን ክፍል ከውስጥ በመቆለፍ ያለምንም ውጣ ውረድ ካሰበበት ስዊዘርላንድ መግባቱንና ፖለቲካ ጥገኝነት እንደሚፈልግ ባካባቢው ለነበሩት የስዊዘርላንድ ፖሊሶች መግለጹን ተያይዞ የመጣው መረጃ ያስረዳል።

የአውሮፕላኑ ምክትል አብራሪ በማንኛውም ጊዜ ወደ ፈለገው ሀገር በመውጣት ሾልኮ የመቅረት እድሉ እጅግ ከፍተኛ እንደነበር የሚገልጹ አንዳንድ ታዛቢዎች ”አብራሪው እንዲያበረው ቁልፉን የተረከበውን አውሮፕላን መጥለፉ ጀግና እንደማያሰኘው በደንብ ያውቃል በማለት ግምታቸውን ይገልጹና እንዲህ አይነቱ ድርጊት በአሳማኝ ምክንያት ካልተደገፈ ደግሞ በተያዘበት ሀገር ለአመታት እስር እንደሚዳርግ አሳምሮ የሚያውቀው ምክትል አብራሪ ታዲያ ለምን በዚህ መልኩ ከሀገር ለመውጣት ፈለገ?” በማለት ራሳቸውን ከተየቁ በኋላ እንደገና በመቀጠል ”በራሱ ላይ የመጣውን ለመቀበል የወሰነው ይህ ምክትል አብራሪ ለዓለም ማሕበረሰብ ማስተላለፍ የፈለገው በፋሽስት ወያኔ ላይ ያለውን ተቃውሞ ማሳየት ነው” ይላሉ።

( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የፋሽስት ወያኔ ከጅቡቲ መቀሌ ባቡር ሃዲድ ግንባታ ወሬ ብዙዎቹን እያነጋገረ መሆኑ ተሰማ

ከጅቡቲ መቀሌ ይገነባል እየተባለ ላለፉት ሁለት ሶስት አመታት በሰፊው ሲናፈስ የነበረው ወሬ ሌሎች አጃቢ የባቡር ሃዲድ ግንባታዎችን ጨምሮ ሰሞኑን በወያኔ ውሸት ዜና ማሰራጫዎች መገለጹ ታውቋል።

የትራንስፖርት አገልግሎትን ጨምሮ ሌሎችም መሰረተ ልማቶች ላንዲት ሀገር እድገት ወሳኝ መሆናቸውን የሚገልጹ አንዳንድ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ግለሰቦች ”እንዲህ አይነቶቹ ትላልቅ የትራንስፖርት አውታሮች ባንድ አካባቢ የሚመረትን የተትረፈረፈ ምርት እንዲሁም የማእድን ውጤቶች ወደ ሌሎች አካባቢዎች ወይም ወደ ዓለም ገባያ ለማድረስ አሌ የማይባል አገልግሎት እንዳላቸው ይገልጹና የትግራይ ክልል ግን ከራሱ ተርፎ ለውጭ ወይም ለሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች አምርቶ የሚያቀርበው የምርት አቅም እንደሌለው በማስታወስ የባቡር ሀዲድ ግንባታው በቀጥታ ወደ መቀሌ ከሚሆን ይልቅ ወደ መሃል ሀገር ቢሆን አዋጭ ነበር ይላሉ።

ከመጠን በላይ የተትረፈረፈ ምርት በማምረት የሚታወቀው ደቡብ፣ መእራብ፣ ሰሜን ምእራብና መሃል ኢትዮጵያ የዚህኛውን የባቡር ሃዲድ ግንባታ ያህል ትኩረት እንዳልተሰጠው አጽንኦት ሰጥተው የሚገልጹት እነዚህ ታዛቢዎች ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል በሚል ስጋት ብቻ ግን አጃቢ የባቡር ሃዲድ ግንባታ እቅድ እንዲቀመጥላቸው ተደርጓል ይላሉ።

ሌሎች ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ ታዛቢዎች ደግሞ ፋሽስት ወያኔ በትግራይ ክልል የተነሳበትን፤ ካቅም በላይ ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## ጎንደር ዉስጥ ታክሲ ሹፌሮች የስራ ማቆም አድማ መቱ

የጎንደር ከተማ ትራፊክ ጽ/ቤት በቅርቡ ያወጣዉን አዲስ የትራፊክ የቅጣት ደንብ በመቃወም ጎንደር ከተማ ዉስጥ የሚገኙ ታክሲዎች የስራ ማቆም አድማ ማድረጋቸዉን ጎንደር ከተማ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢዎች በላኩልን ዜና ገለጹ። የታኪሲ ሾፌሮች አድማ በመቱበት ቀን በተለያዩ የከተማይቱ አደባባዮች ላይ በብዛት ሆነዉ አንድ ላይ በመንዳትና ጥሩምባቸዉን ከፍ አድርገዉ በማሰማት ተቃዉሟቸዉን ሲያሰሙ ዉለዋል። ይህ ከሆነ ከጢቂት ግዜ በኋላ ታክሲአወቹ አንዳሉ ወዳልታወቀ ቦታ ሄደዉ በመሰወራቸዉ የከተማዋ የታክሲ ተገልጋዮች ነዋሪዎች ታክሲዎችን ለማግኘት ሲቸገሩ ታይቷል።

አንዳንድ የገዢው ፓርቲ ደጋፊዎችና ሲቪል የለበሱ የጸጥታ ሰራተኞችና የትራፊክ ፖሊሶች በየመንገድ ላይ ያገኙትን ታክሲ በማስገደድ ሰዎችን እንዲጭን ለማድረግ መሞከራቸዉንና ፈቀደኛ ያለሆኑ ሾፌሮች ያስፈራሩ እንደነበር ለማዉቅ ተችሏል።ይህንን ዜና እስካጠናቅርንበት ግዜ ድረስ አድማዉ የቀጠለ ሲሆን ምን ያህል አንደሚቀጥል የታወቀ ነገር የለም።

በሌላ በኩል በነዳጅ ምርቶች ላይ ሰሞኑን የተጣለው እጅግ ከፍተኛ ጭማሪ በቋፍ ላይ የሚገኘውን የህብረተሰቡን ኑሮ ይበልጥ አስከፊ እንዳደረገው የኢሳት የ አዲስ አበባ ሪፖርተር ዘግቧል።በቤንዚን ምርቶች ላይ በ አንድ ሊትር እስከ 45 ሳንቲም፣ ለማገዶነት በሚውለው በኬሮሲን ምርት ላይ በ አንድ ሊትር እስከ 75 ሳንቲም የተጣለው የሰሞኑ ይፋዊ ያልሆነጭማሪ፣ በነዳጅ ጭማሪ ታሪክ እጅግ አስደንጋጭና ከፍተኛ ጭማሪ እንደሆነ ነዋሪዎች በምሬት እየተናገሩ ነው። የታክሲ ትራንስፖርት አገልግሎት ከ0.5 ሳንቲም እስከ 0.15 ሳንቲም ጭማሪ ተደርጎበታል።ሀቁ ይህ በሆነበት ሁኔታ የመንግስትና የድርጅት ሚዲያዎች አስደንጋጩን የነዳጅ ጭማሪ “መጠነኛ ጭማሪ” እያሉ ሲያወሩ መሰማታቸው፤ በህብረተሰቡ ቁስል ላይ ተጨማሪ እንጨት እንደመስደድ ነው ይላሉ ነዋሪዎቹ።

## 77ኛው የሰማዕታት ቀን ታስቦ ዋለ

ወራሪዎቹ የሙሶሎኒ ወታደሮች ሰላማዊ ኢትዮጵያዉያዉንን በግፍ የጨፈጨፉበት 77ኛዉ የሰማዕታት ቀን ባለፈዉ ረቡዕ ዬካቲት 12 ቀን 2006 ዓም በአለም ዙሪያ ኢትዮጵያዉያን በሚገኙበት ቦታ ሁሉ ታስቦ መዋሉን በየቦታዉ የሚገኙት ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። በዓሉ ጭፍጫዉ በተካሄደባት አዲስ አበባ ዉስጥ በልዩ ሁኔታ ታስቦ የዋለ ሲሆን ስድስት ኪሎ ዉስጥ በሚገኘዉ የሰማዕታት መታሰቢያ ኃዉልት ስር አበባ በማስቀመጥ ጀአግኖች አባት አርበኞች ለበዓሉ ልዩ ድምቀት ሰጥተዉታል። የካቲት ፲፪ ቀን ፋሽስት ኢጣሊያ ጦር በአዲስ አበባ እና በሌሎችም ዋና ዋና የኢትዮጵያ ከተሞች በ፲ሺህዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን በአሠቃቂ ሁኔታ የጨፈጨፈበትን ግፍና በደል የምናስታውስበት ዕለት ነው። በዚህች አሳዛኝ ቀን በኢጣሊያን ፋሽስቶች የጦር መሪ ጄኔራል ሮዶልፎ ግራዚያኒ ትዕዛዝ፣ በሶስት ቀናት ውስጥ ብቻ ከ፴ሺህ የማያንሱ ንፁሃን ኢትዮጵያውያን የተጨፈጨፉበት ድርጊት የተጀመረበት ነበር። የ1929ኙ የፋሺስት ጣሊያን ጭፍጨፋ የተካሄደዉ አዲስ አበባ ዉስጥ ጀግኖች ኢትዮጵያዉያን ከወራሪዉ ኃይል ጋር በሚተናነቁባቸዉ በደብረሊባኖስና በዝቋላ ገዳማት፣ በፍቼ፣ በደብረብርሃን፣ በደብረማርቆስ ና በሌሎችም የኢትዮጵያ ከተሞች፣ በአርበኝነት ትግል ይሣተፋሉ ተብለው የሚጠረጠሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እየተለቀሙ ተፈጅተዋል።

( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## የኢትዮጵያዊዉ ፓይለት የሃይለመድህን አበራ ጉዳይ የአለማችን የዜና ማሰራጫዎችን ዋና የመነጋገሪያ አርዕስት ሆኖ ሰነበተ

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ ቁጥር 702 የሆነውን አውሮፕላን በመጥለፍ ጄኔቫ ስዊዘርላንድ ያሳረፈው ረዳት ፓይለት ሃይለመድህን አበራ እስካሁን ድረስ የጠለፋውን መንስኤና ምክንያት በግልጽ አብራርቶ የመናገር እድል ባለማግኘቱ የአለም የመገናኛ ብዙሃንን ጨምሮ የተለያዩ አስተያየቶችን እየተሰጡ ነው። እየተሰጡ ካሉት አስተያየቶች ሚዛን እየደፋ የሚገኘው ግን ሃይለመድህን አበራ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ ያለው አይን ያወጣ ዘረኝነት፣ በደልና ሙስና እጅግ በመማረሩ የወሰደው እርምጃ ነው የሚለው ሲሆን፡ የራሱን ጥቅም እና የተደላደለ ኑሮ ትቶ የህዝቡን ብሶትና ሰቆቃ ለአለም ህዝብ ትኩረት እንዲያገኝ ማድረግ ያስቻለ ስለሆነ ክብር ይገባዋል በማለት እርምጃውን እያወደሱ ይገኛሉ። ከዚህ በፊት ባልተመደ ሁኔታ የአለም መገናኛ ብዙሃን ስለ ኢትዮጵያ ህዝብ መከራና ችግር በትኩረት እንዲወያዩ አድርጓል፡ ከ500 በላይ አለማቀፍ ጋዜጦች ፊታቸውን ወደ ኢትዮጵያ እንዲያዞሩና ስላለው ግፍና ጭቆና በመመርመር

( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የመከላከያ ተቋም ተግባር አገርን መጠበቅ ነዉ ወይስ አገርን መዝረፍ?

የአዉሮፓ ቅኝ ገዢዎች አፍሪካን ሲቀራመቱ ባህር ተሻግረዉ በመጡ የነጭ ባዕዳን ኃይሎች መገዛትን መርጦ የአዉሮፓን ወራሪዎች በሰላም በሩን ከፍቶ ወደ አገሩ ያስገባ እንድም የአፍሪካ አገር አልነበረም፤ የኋላ ኋላ ተሸንፈዉ በቅኝ አገዛዝ ቀንበር ስር ቢወድቁም ሁሉም የአፍሪካ አገሮች እንደ አቅማቸዉ ከወራሪ ኃይሎች ጋር ተፋልመዋል። በአንድ ወቅት የቅርብ ጎረቤቶቻችንን ጨምሮ ብዙዎቹ የአፍሪካ አገሮች በወራሪ ኃይሎች ተሸንፈዉ የቅኝ ገዢዎች ቀንበር ጀርባቸዉ ላይ ሲጫን አገራችን ኢትዮጵያ ብቻዋን የአለም ጥቁር ህዝቦች የነፃነት ተምሳሌት ሆና የኖረችዉ ጣሊያኖች፤ እንንግሊዞችና ፈረንሳዮች ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ለይተዉ ስለወደዷት ወይም ስላከበሯት አይደለም። ይልቁንም ነፃነታችንና የግዛት አንድነታችን ተከብሮ የኖረዉ ኢትዮጵያ እናት አገሩ በጠላት ስትደፈር ከሚያይ ምትክ የሌላት ህይወቱ ብታልፍ ደስ የሚለዉ የኩሩና የጀግና ህዝብ አገር በመሆኗ ነዉ። የሚገርመዉ ይህ ኩሩና ጀግና ህዝብ ጣሊያንን የመሰለ በዘመናዊ መሳሪያ የታጀበ ኃይል ዉርደቱን ተከናንቦ ወደመጣበት እንዲመለስ ሲያስገድድ እንደ ዛሬዉ የተደራጀ ዘመናዊ የመከላከያ ሰራዊት አልነበረዉም። ዛሬ አራት ኪሎና ስድስት ኪሎ ላይ የተተከሉት ሁለቱ ታሪካዊ ሀዉልቶቻችን የሚነግሩንም ይህንኑ የኢትዮጵያ ህዝብ በዘመናዊ መልክ የተደራጀ ሠራዊት ሳይኖረዉ የጎበዝ አለቃ እየመረጠ በጣሊያን ፋሺስቶች ላይ የተጎናጸፈዉን አኩሪ ድል ነዉ።

ኢትዮጵያ ዉስጥ ዘመናዊና የተደራጀ መከላከያ ሠራዊት ጥንስስ የተጣለዉ በዳግማዊ ሚኒልክ ዘመነ መንግስት ሲሆን እሱም ቢሆን ከአድዋ ድል በኋላ ቆይቶ የመጣ ክስተት ነዉ። በአፄ ኃ/ሥላሤና በደርግ ዘመነ መንግስት ኢትዮጵያ ለአንድ ፓርቲና ይህ ፓርቲ እወክለዋለሁ ለሚለዉ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ሙያዊ ብቃት የነበረዉ፤ሙያዉን የሚያከብርና ለአገሩና ለወገኑ ታማኝ የሆነ የመከላከያ ሠራዊት ነበራት። የወያኔ ዘረኞች አዲስ አበባን ሲቆጣጠሩ የመጀመሪያ ኢላማቸዉ አድርገዉ ካወደሟቸዉ ዋና ዋና የአገራችን ተቋሞች ዉስጥ የመጀመሪያዉ ይሄዉ የአገርና የህዝብ ደጀን የነበረዉ ተቋም ነበር። ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ የአገር መከላከያ ሠራዊት እየተባለ የሚጠራዉ ተቋም ለጎጠኞች ጥቅምና የስልጣን መራዘም የቆመ፤ በዘረኝነት የተካፋፈለ፤ ይህ ነዉ ተብሎ የሚጠቀስ ሙያዊ ብቃት የሌለዉና የወገንና የአገር ፍቅር እንዳይኖረዉ ተደርጎ የተደራጀ ሰራዊት ነዉ። ይህንን ሠራዊት የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ሳይሆን የወያኔ ሠራዊት እያልን የምንጠራዉም በዚሁ ምክንያት ነዉ።

ዛሬ ሙሉ በሙሉ በወያኔ ዘረኞች ቁጥጥር ስር የወደቀዉ የአገር መከላከያ ተቋም የሚታማዉ በዘረኝነት፤ በሙያ ብቃት ማነስና የአንድ ፓርቲ ጥቅም አስከባሪ በመሆኑ ብቻ አይደለም፤ ተቋሙ ከእነዚህ ዋና ዋና ጉድለቶቹ በተጨማሪ በቀድሞዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ተቋም ላይ በፍጹም ያልታዩ ሌሎች ትላልቅ ጉድለቶች አሉበት። ከእነዚህ ጉድለቶች ዉስጥ አንዱ የወያኔ የመከላከያ ተቋም ህገ መንግስቱ ከሰጠዉ ኃላፊነት ዉጭ በንግድና በንብረት ይዞታ ላይ ላይ መሰማራቱ ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ ከዚህ ፀባዩ ጋር ተያይዞ በመከላከያ ሠራዊት ተቋም ዉስጥ ከላይ እስከታች የሰፈነዉ ቅጥ ያጣ ሙሰኝነት ነዉ። ዛሬ የወያኔን የመከላከያ ተቋም፤ የህወሀትን ፓርቲና ኤፎርት በሚል ምህጻረቃል የሚታወቀዉን የወያኔን የገንዝብ ማምረቻ ድርጅት ነጣጥለን ወይም አንዱን ከሌላዉ ለይተን ማየት የማንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል።

በላፈዉ አመት ወያኔ እራሱ ያቋቋመዉ ፀረ ሙስና ኮሚሺን የገንዘብ ዝርፊያን፤ የንብረት መባከንንና መዝረክረክን አስመልክቶ ለፓርላማዉ ባቀረበዉ ሪፖርት ላይ ከጠቀሳቸዉ መንግስታዊ ተቋሞች ዉስጥ ቀዳሚዉን ደረጃ የያዘዉ የመከላከያ ተቋም ነዉ። ሆኖም ፓርላማዉም ሆነ የወያኔ አገዛዝ ለዚህ ሪፖርት የሰጡት ምላሽ የመከላከያና የደህንነት ተቋሞች ከአሁን በኋላ ያሻቸዉን ያክል ገንዝብ ቢዘርፉ የሂሳብ መዝገባቸዉ "ለአገር ደህንነት" ሲባል በኦዲት ኮሚሺን አይመረመርም የሚል ምላሽ ነበር። እንግዲህ ይህ በሙሰኝነት የተጨማለቀ፤ ለህግ የማይገዛና መጠበቅና መንከባከብ የሚገባዉን የአገር ኃብትና ንብረት የሚዘርፍ ተቋም ነዉ ባለፈዉ ሳምንት "የመከላከያ ቀን" ተብሎ አመታዊ በዐል የተከበረለት።

መናገሻ ከተማችን አዲስ አበባ ዉስጥ በየቦታዉ የሚታዩትን ሰማይ ጠቀስ ህንፃዎች ሰርተዉ የሚያከራዩት የወር ደሞዛቸዉ ከ2500 ብር የማይበልጥ መከላከያ ሠራዊት ዉስጥ የተሰገሰጉ የወያኔ ጄኔራሎች ናቸዉ፤ ኢትዮጵያ ዉስጥ ትርፋማ በሆኑ ቦታዎች ሁሉ ትላልቅ ሆቴሎች፤ የአገልግሎት ተቋሞችና የንግድ ድርጅቶች ከፍተዉ ቁጥር ስፍር የሌለዉ ኃብት የሚያጋብሱት የወያኔ ጄኔራሎች ናቸዉ፤ ድሃዉና የወያኔ ዘረኝነት ሰለባ የሆነዉ ኢትዮጵያ ሰራዊት ለተመድ ተልዕኮ በተሰማራባቸዉ ቦታዎች ሁሉ ተመድ የሚከፍለዉን የቀን አበል ኪሳቸዉ ዉስጥ እየከተቱ ሚሊዮነሮች የሆኑትና በየዉጭ አገሩ ዉድ መኖሪያ ቤቶችንና የንግድ ተቋሞችን የሚገዙት የወያኔ ጄኔራሎች ናቸዉ። የወያኔ መከላከያ ተቋም ጉድ በዚህ ብቻ አያበቃም፤ ይህንን ወንጀለኛ ተቋም ቃላት እየደረደሩ ለመግለጽ ከመሞከር ይልቅ በጥቅሉ ወያኔ የኢትዮጵያን ህዝብ ኃብትና ንብረት እንዳሻዉ መዝረፍ እንዲችል የኃይል ሽፋን የሚሰጥ ተቋም ነዉ ማለት የሚበቃ ይመስለናል።

ወያኔና ስር የሰደደዉ ዘረኛ ስርዐቱ ከኢትዮጵያ ምድር ላይ እስካልተነቀሉ ድረስ ወያኔ ዝርፊያዉን የወያኔ መከላከያ ተቋምም የወያኔንና የደገፊዎቹን ዝርፊያ በመሳሪያ ማጀቡ አይቆምም። የወያኔን ዝርፊያ ለማስቆምና አገራችንን ከተጋረጠባት አሳሳቢ አደጋ ለመታደግ ብቸኛዉ መንገድ ወያኔን ከሥልጣን ማስወገድ ብቻ ነዉ። ግንቦት 7 የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የጀመረዉ ህዝባዊ ትግል እንደ አገር መከላያከያ አይነቶቹ ቁልፍ የአገር ተቋሞች በሚሰሯቸዉ ስራዎች ሁሉ የአገርንና የህዝብን ጥቅም እንዲያስጠብቁ ለማድረግ ነዉ። የግንቦት 7 ትግል አላማ የመከላከያ፤ የደህንነት፤ የፖሊስና የፍትህ ተቋሞች የአንድ ፓርቲ ጥቅም ማስከበሪያ መሳሪያዎች መሆናቸዉ አብቅቶ የአገርና የህዝብ አለኝታ እንዲሆኑ ነዉ፤ ሆኖም ይህንን ቅዱስ አላማ ወያኔ በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ ተግባራዊ ማድረግ ስለማይቻል ነፃነት፤ ፍትህ፤ዲሞክራሲ፤ ሠላምና እኩልነት የናፈቀዉ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ወያኔን በፍጥነት እናስወግድ ከሚለዉ የአገር አድን አላማ ጎን እንዲሰለፍ ግንቦት 7 የትግል ጥሪዉን ያስተላልፋል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን በራሱ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ፋሽስት ወያኔ እየደረሰበት ያለውን በሕዝብ መተፋት በውሸት ሪፖርቶች ለመሸፋፈን ትላልቅ ድርጅቶችን ጨምሮ ሌሎችንም መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች በመምራት አቅምና በቂ ልምድ ያላቸውን ሰራተኞች በማባረር አድርጉ የሚባሉትን ብቻ በሚያደርጉ የራሱ ታማኝ ሰዎች የተቆጣጠረ ሲሆን የኢትዮጵያ አየር መንገድን ለታላቅ ዝና ያበቁትን ታዋቂ አብራሪዎችንም እያባረረ የውጭ ዜግነት ባላቸው አብራሪዎች እየተካ መሆኑ በተደጋጋሚ ሲዘገብ መቆየቱ ይታወሳል። በማንኛውም ሰአት ወደፈለገው ሀገር በሰላም መሄድ ሲችል በዚህ መልኩ እንዲከወን የፈለገው የዛሬው የአውሮፕላን ጠለፋ ድራማም ከዚሁ ጋር የተያያዘና ይህንን የተዛባ የወያኔ ሕወሃት ስራ ለማጋለጥ የተደረገ ሲሆን እንደሚችል የሚተቅሱ ትቂቶች አይደሉም።

ከዚህ በፊትም እንደዛሬው የአውሮፕላን ጠለፋ በዓለም ደረጃ በስፋት አይታወቁ እንጅ በመቶዎች የሚቆጠሩ መምህራን፣ የህክምናና የግብርና ባለሙያዎች፤ ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ ከራሱ ከወያኔ ሕወሃት ጋር ሲሰሩ የነበሩ ሰራተኞች እንዲሁም ባለሌላ ማእረግ ጀኔራሎች፣ ኮሌኔሎችና ቁጥራቸው በጣም ብዙ የሆነ ተራ ወታደሮች አገዛዙ አንገሽግሿቸው ሀገራቸውን እየጣሉ በመሰደድ በየደረሱበት ሀገር የፖለቲካ ጥገኝነት ጥያቄ እየጠየቁ መሆኑና የሚበዙት ደግሞ ወያኔ ሕወሃትን ለመዋጋት ከተቃዋሚ ሃይሎች ጋር በመቀላቀል ላይ እንደሚገኙ በተለያዩ ሚዲያዎች መዘገቡ አይዘነጋም።

የተጠልፈው አውሮፕላን ጀኔቭ ማረፉን ከተለያዩ ዓለማቀፍ የዜና አውታሮች ማረጋገጡን ያልካደውና ዜናውን በምስል አስደግፎ የዘገበው ውሸት የማይሰለቸው የወያኔ ሕወሃቱ ቴሌቪዥን ጣቢያ ግን "በረራ ቁጥር 702 አውሮፕላንን ለመጥለፍ የተደረገው ሙከራ ከሸፈ" በማለት የከሸፈ ዜና አሰራጭቷል። ጠላፊው የጠለፈውን አውሮፕላን አቅጣጫ አስቶ ይዞ በመሄድ ከፈለገበት ቦታ ወስዶ ማሳረፍ ከቻለ እንዴት ነው ጠለፋው ከሸፈ የሚባለው የሚሉ አንዳንድ ታዛቢዎች ምናልባት ወያኔ ሕወሃት አውሮፕላኑ ተጠለፈ ይል የነበረው አውሮፕላኑ ተከስክሶ ሂዎት ቢተፋ ይሆን? በመለት ስላቃዊ ትዝብታቸውን ቋጭተዋል።

በወያኔ ሕወሃት ዘርን መሰረት ያደረገ አገዛዝ ምክንያት ኢትዮጵያን በዓለማቀፍ ደረጃ ያስተዋውቁ የነበሩ እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ያሉ አትራፊ ድርጅቶች በፊት የነበራቸውን ትርፍና ብቃት መመለስ የተሳናቸው ሲሆን ባሁኑ ሰአትም አየር መንገዱ አመጣው የሚባለው ገቢ እንደ ድርጅት ለሕወሃትና አሉ ለሚባሉ የሕወሃት ቁንጮዎች ኪስ ባዳጎሻነት እየዋለ መሆኑ በተደጋጋሚ መዘገቡ ይታወሳል።

---

## ወርሃ የካቲት

በአገራችን ታሪክ ውስጥ ወርሃ የካቲትን ልዩ የሚያደርጓት ቁም ነገራት አሏት። አስቀድመን ጀግኖቹ አብርሃ ደቦጭ እና ሞገስ አስግዶም ግሪያዚያንን ያስበረገገውን ቦንብ ያፈነዱበት ወር የካቲት መሆኗን ማስታወስ እንወዳለን። በዚህ ምክንያትም በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ከ30 ሺህ በላይ ህዝብ ተገድሎ የሰው ደም እንደ ክረምት ጎርፍ ከተማዋን ያጥለቀለቀው በዚህች በየካቲት ወር ነው። በሌላ በኩል ጠላቴ *"የአማራ ህዝብ እና ተፈጥሮ ኀው* ብሎ በፅኑ የሚያምነው ህወሃት የተወለደው በወርሃ የካቲት ነው። የየካቲት ታሪክ በዚህ ብቻ አያበቃም በወርሃ የካቲት ህወሃት "የመከላከያ ኃይል ቀን " እያለ ከበሮውን እየደለቀ የሚድሪቷ ከርስ እስከሚበረበር ድረስ ዳንኪራ ይረግጣል።

ለብዙ ኢትዮጵያዊያን ግን የካቲት የደስታ ወር አይደለችም። የካቲት በግፍ የተገደሉብንን ዜጎቻችንን እያስታወስን ልቦናችን በሃዘን የሚታወክበት እንጂ ሃሴት የምናደርግበት ወር አይደለችም። በየካቲት ወር ግራዚያን *"ያገኛችሁትን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ግደሉ"* ብሎ አዋጅ በማስነገሩ በጭካኔው የምንቆጣበት እንጂ በደስታ የምንሰክርበት ወር አይደለችም። በወርሃ የካቲት የሌላውን ቦታ ሳይጨምር በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ከ30ሺህ በላይ ኢትዮጵያዊያን ሲጨፈጨፉ ከግራዚያን ጎን ቁመው ወገኖቻቸውን ያስጨፈጨፉ ባንዳዎችን እያሰብን አንገታችንን ደፍተን የምናዝንበት ወር እንጂ የደስታ ወር አይደለችም። ወርሃ የካቲት ለኢትዮጵያዊያን በደግ የምትታወስ ወር አይደለችም። በወርሃ የካቲት የተወለደው ህውሃት የተባለው ዘረኛና ዘራፊ ቡድን በአገራችን ላይ ያደረሰውን ግፍ እያሰብን ግፉ እንዲያበቃ አእምሯችን የምንሰበስብበት ወር ነች። ህወሃት በመወለዱ ኢትዮጵያችን የድሆች ሁሉ ድሃ፤የደካሞች ሁሉ ደካማ፤ ልትበታተን አደጋ አፋፍ ላይ ያለች አገር ተብላ ሥሟ በበጎ የማይነሳ አገር እንድትሆን ሆነች።

ህወሃት በወርሃ የካቲት ተወለድኩ ሲል አወጀ። ከዚያም ቀጥሎ እንዲህ አለ *"አማራና ተፈጥሮ ጠላቶቼ ናቸው"* ሲል ድምፁን ከፍ አድርጎ ጮኸ። ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ የሚያምን ከተገኘም አሸባሪ እና ትምክህተኛ ነውና ይገደል ሲል ያልተፃፈ ህግ አፀደቀ። በየካቲት ወር ይህን የሞት ድምፅ ብዙ ዜጎች በአርምሞና በግርምት ሰሙት። ህወሃት አገሪቷን ክተቆጣጠር በኋላ ከሁለት ሚሊዮን በላይ አማራ የገባበት አልታወቀም ተብሎ ለፓርላማ መሰል አካሉ ሪፖርት ቀረበ። በግራዚያን አዋጅና በህወሃት አዋጅ መካከል ልዩነት የለም። በየካቲት ወር ግራዚያን "ያገኛችሁትን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ግደሉ" ብሎ የሞት አዋጅ አወጀ። በዚህ አዋጅ ምክንያት በአንዲት ጀንበር 30ሺህ ኢትዮጵያዊያን በአዲስ አበባ ተፈጁ። ግዲያውን ለማስፈፀም ከፊቱ የቀደሙ በስም ኢትዮጵያዊን በምግባር ግን ፋሽት የሆኑ ምናምንቴዎች ነበሩ። ከእነዚህ ውስጥ የመለስ ዜናዊ እና የስብሃት ነጋ ወላጆች በፍፁም የሚረሱ አይሆኑም። እነዚህ የባንዳ ውላጆች በወርሃ የካቲት "አማራና ተፈጥሮ ጠላቶቼ ናቸው" ብለው አውጀው ህወሃትን መሥርተው ለስልጣን ከበቁ በኋላ 2ሚሊዮን አማራ ጠፋ። በወርሃ የካቲት የተወለደው ህወሃትና ፋሽስቶችን ከሚያመሳስለው ድርጊት መካከል አንዱ ይሄው ነው። በየካቲት የተወደው ህወሃት ኢትዮጵያን በመከራ አረንቋ ውስጥ ደፍቆ እስከ ዛሬ ዘለቀ። በዚህ ምክንያት ወርሃ የካቲት ለኢትዮጵያዊያን ደገኛ ወር አይደለችም።

በኢትዮጵያዊያን ታሪክ ውስጥ የካቲት የምትታወስበት ሌላ አብይ ነገር ደግሞ አለ። አብርሃም ደቦጭና፤ሞገስ አስግዶም የተባሉ ከኤርትራ የመጡ ወጣቶች የኢትዮጵያ ጠላት በሆነው በግራዚያን ላይ የፈፀሙት ጀግንነት ነው። እነዚህ ሁለት ወጣቶች በጨካኙ ግራዚያኒ ላይ በወረወሩት ቦንብ በፋሽስቶቹ መንደር ጉዳት አደረሱ። ይሄ ድርጊት በአርበኝነት ተሠማርተው ለነበሩት ጀግኖች አበረታች ድርጊት እንደነበረ በታሪክ ተመዝግቧል። ከዚህ ድርጊት በኋላ ግን በሦስት ቀን ብቻ በአዲስ አበባ ከተማ ከ30ሺህ በላይ ህዝብ ተገደለ። በዚሁ በየካቲት ወር አብርሃምና ሞገስ አልፈውበታል በተባለው በደብረ ሊባኖስ ገዳም የተገኙ 297 መናኞች እና ሌሎች 23 ኢትዮጵያዊያን በአንዲት ጀንበር እንዲገደሉ ተደረገ። ይሄ ሁሉ ግዲያ ሲፈፀም ቀላል የማይባሉ ባንዳዎች አብረው ከግራዚያን ጎን ቁመው ነበር። እንዲህ ዓይነቱን አሰቃቂ ድርጊት እንዲፈፀም ትእዛዝ የሰጠው ግለሰብ ሃውልት በአደባባይ ይሠራለትና ሥሙም ለዘላለም ይታወስ የሚሉ የፋሽት አቀንቃኞች በተነሱ ግዜ ህወሃቶች ዝምታን መረጡ። እንዲያውም የፋሽቶች ሃውልት በአደባባይ እንዳይቆም ለመቃወም የተነሱ ኢትዮጵያዊያንን በቆመጥ እየደበደቡ የተቃውሞው ድምፅ እንዳይሰማ ሰልፉን በማፈን ለፈሽቶች ያላቸውን ክብር አስመስከሩ። ከወርሃ የካቲት ትዝታዎቻችን መካከል መታወስ ያለበት አንዱ የህወሃት መልክ ይሄው ከፋሽስቶች ጋር የመደጋገፍ ድርጊቱ ነው።

ወርሃ የካቲት ሌላም ገፅታ አላት። በዚህች በየካቲት ወር ህወሃቶች የመከላከያ ቀን እያሉ በስካርና በፈንጠዝያ ያከብራሉ። ኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል ከገነባችም ሃያ አንድ ዓመት ሞላት እያሉም ይዘባትላሉ። እውነቱ ግን አገራችን ኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊቷን ካጣች ሃያ አንድ ዓመት መቆጠሩ ነው። በዘመነ ህወሃት ኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አላት ለማለት በሚያስችል ሁኔታ ላይ የምትገኝ አገር አይደለችም። ብዙ መልክ እና ባህል ባላቸው ዜጎች በቆመች አገር ውስጥ አጠቃላይ የመከላከያ ሠራዊቱ አዛዦች ከአንድ ወንዝ የተቀዱ ፤ከአንድ መንደር የተሰባሰቡ ስለመሆናቸው ቀደም ብለን ያወጣነውን መረጃ ማየት ይረዳል። የእነዚህ ቡድኖች ከአንድ ወንዝ መቀዳታቸው፤ ከአንድ መንደር መሰባሰባቸው ችግር አይደለም፤ችግሩ የሚነሳው ግለሰቦቹ ፍፁም ኃላፊነት የማይሰማቸው፤በአፍቅሮተ ንዋይ የታወሩ፤የአገርና የወገን ፍቅር የሌላቸው ፍፁም ጨካኝና ክፉ ዘረኞች ሁነው የመገኘታቸው ነገር ነው አገሪቷን ውሉ ከማይታወቅ ችግር ውስጥ የዘፈቃት። ዛሬ ካርታ ይዘው የቆሙበትን ሥፍራ ለማሳየት የሚደናበሩ ጄኔራሎች ባለሚሊየን ዶላር ሃብት ባለቤት የመሆናቸው ነገር አገሪቷ ከተጋረጡባት ችግሮች መካከል አንዱ ነው። የመከላከያ ቀን ሲከበር የጦሩ አለቆች ከአንድ ምንጭ የተቀዱ ዘራፊዎች፤ነፍሰ ገዳዮችና፤ አለሰፋራቸው ሚሊየነር ነጋዴ ሁነው የመገኘታቸው ነገር አብሮ መታወስ ይኖርበታል።

በየካቲት ወር የመከላከያ ቀን ሲከበር አብረን የምናስታውሳቸው ሌሎች አሳዛኝ እውነቶች ደግሞ አሉ። ከብዙዎቹ ጥቂቶቹን ለማስታወስ ያክል የአገሪቷ መከላከያ ሠራዊት በሠላም አስከባሪ ሥም ሶማሊያ ድረስ ዘልቆ ገብቶ የሚሞትበትንና የሚገድልበትን ምክንያት ዜጎች የማወቅ መብት የላቸውም መባሉን ከመከላከያ ኃይል ቀን አከባበር ጋር አብረን የምናስታውሰው ጉዳይ ይሆናል። ከዚህ ጋር ተያይዞ መታወስ ያለበት እውነት ደግሞ በሠላም አስከባሪ ሥም የህወሃት ጄኔራሎች እየተፈራረቁ በየቀኑ ከ160 ዶላር በላይ ዓበል የመሰብሰባቸው ጉዳይ ነው። ጄኔራል ተብየዎች በየቀኑ ከ160 ዶላር በላይ ሲያጋብሱ ድሃው ወታደር ግን ለምንና ለማን እንደሚሞት ሳያውቅ በወጣበት ይቀራል። አስከሬኑም ክብር አጥቶ በሶማሌ ጎዳናዎች ላይ እየተጎተተ መሳቂያ መሳለቂያ ይሆናል። የህወሃት ጄኔራሎች ግን በዚህ ሁኔታ ዜጎችን እያስፈጁ ለሦስት ወታደር በወር የሚከፈለውን ደሞዝ በየቀኑ ወደ ኪሳቸው እየከተቱ በደስታ ይሰክራሉ።

የመከላከያ ኃይል ቀን ሲዘከር አብረን የምናስታውሰው በአገሪቷ ሥም የተቋቋመው ሠራዊት የገዛ ዜጎቹን ያለ ርህራሄ የሚገድል፤ አጋዴን ወርዶ ዘር የሚያጠፋ፤ጋምቤላ ወጥቶ ያገኘውን ሁሉ የሚገድል፤አዲስ አበባ ላይ ከተማሪ ቤት የሚመለስ ህፃንን ሳይቀር ተኩሶ ለመገድል የማይራራ። የሚፈፅመውን የጭካኔ ድሪጊት ከትክክለኛ ኃላፊነቱ ጋር ደባልቆ የሚያይ ቡድን መሆኑንም አብረን ማስታወስ አለብን። ይሄ ሠራዊት ተብሎ የሚጠራው ቡድን ሊጠብቀው የሚገባውን ህዝብ እንዲያሸብርና እንዲገድል ሁኖ የተቀረፀው በህወሃቶች እኩይ አመራር መሆኑንም በየካቲት ወር ከሚከበረው የመከላከይ ቀን ጋር አብረን እናስታውሳለን።
ወርሃ የካቲት የህወሃት የውልደት ወር፤የግራዚያን የግፍ ግዲያ ወር፤የህወሃት መከላከያ ኃይል የሚከበርባት ወር በመሆን እየታወሰች ነው። የካቲት በአገራችን ላይ የሃዘን ድባባ ያጠላባት ወር እንጂ ከበሮ የሚመታባት፤ ዳንኪራ የሚረገጥባት ወር የምትሆን አይደለችም። ህወሃቶች ግን ይህችን ወር እየጠበቁ ከበሯቸውን እየደቁ፤ የምድሪቷ ከርስ እስከሚበረበር ድረስ ዳንኪራ እየረገጡ ይውረገረጉባታል። ለብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ ግን የካቲት የትካዜ ወር እንጂ የደስታ ወር አይደለችም።

በመጨረሻም ህወሃቶችን እንዲህ እንላችኋለን !

የካቲትን እየጠበቃችሁ ከበሮ የምትደልቁበት ዘመን እንደሚያበቃ አትጠራጠሩ። ህወሃቶች ሆይ! ስሙን ! አገር አልባ አድርጋችሁናል። የአገራችንን ግርማ አጥፍታችሁ፤ዝናዋን አዋርዳችሁ የደካሞች ደካማ፤የርሃብተኞች ርሃብተኛ እንድትሆን አድርጋችኋል። ዜጎች በማይገባቸው ጦርነት ውስጥ ገብተው አለ በቂ እና አሳማኝ ምክንያት እንዲሞቱ አድርጋችኋል። በዜጎች ደም እየነገዳችሁ ብዙ ሚሊየነር ጄኔራሎችን አፍርታችኋል። ዜጎች ኢትዮጵያ ውስጥ ከምንኖር ሂደን የበርሃ ሲሳይ እንሁን፤ የባህር አዞም ይብላን እያሉ እንዲሰደዱ ምክንያት ሁናችኋል። እናንተ በዚህ ሁኔታ ህዝቡን እያስለቀሳችሁ የካቲት በደረሰች ቁጥር ከበሯችሁን እየደቃችሁ በደስታ ትሰክራላችሁ። ይሄ ግን በዚሁ እንደማይቀጥል እኛ እንነግራችኋለን። ደግሞም አትጠራጠሩ፤ በዚሁ አትቀጥሉም። ከእናንተ ጋር ያሉት ሌሎች ግራዚያኒ ያገኛችሁትን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ግደሉ ብሎ ትዕዛዝ ሲሰጥ ከጣሊያን ወታደሮች ለሚወረወርላቸው ፍርፋሪ ብለው ወገኖቻቸውን አሳልፈው እንደሰጡ እንደዚያን ግዜ ባንዳዎች ከማየት የዘለለ የሚባልላቸው ሌላ ነገር የለም። ወገናቸውን ህዝባቸውንና አገራቸውን የካዱ መሆናቸውን እኛ ብቻ ስናሆን ራሳቸውም ጭምር ያውቁታል። ለማንኛውም እናንተም ሆናችሁ ለምናምን ሲሉ ወገኖቻቸውን አሳልፈው የሰጡ የአስቆሮታዊው ይሁዳ ምሳሌዎች ቀናችሁ እየጨለመ መሆኑን ዓይናችሁን ከፍታችሁ እንድታዩ እንመክራችኋለን። አበቃን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

## በባህር ዳር ከፍተኛ ውጥረት ነግሷል፡ ወጣቶችን ማሳደዱና አፈሳው ተጠናክሮ ቀጥሏል

የጉጅሌው ወያኔ የጥፋት ክንፍ የሆነውን ብአዴንን በመቃወም አንድነትና መኢአድ ለየካቲት 16 ቀን 2006 ዓ.ም ሰልፍ መጥራታቸውን ተከትሎ በከተማዋ ከፍተኛ ውጥረት ነግሷል፡ የባጃጅ አሽከርካሪዎች ሰልፉን እንዳይቀሰቅሱና እንዳይሳተፉ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል፡ በጉጅሌው [ስራ አጥ] ተብለው የተፈረጁ ነገር ግን የሃገር ተረካቢ የሆኑ አምራች ወጣቶች በስፋት በቅጥረኛ ፖሊሶች እየታደኑ እየታፈሱ እንደሚገኙ በአካባቢው የሚገኝ ዘጋቢያችን አድርሶናል። ዘጋቢያችን እንዳደረሰን በከፍተኛ ስጋት ውስጥ የሚገኙት ቱባ የብአዴን ባለስልጣናት እንዳስተላለፉት በተነገረለት ቀጭን ትዕዛዝ አማካኝነት በከተማዋ ብዛት ያላቸው ቅጥረኛ የፌደራል ፖሊሶች ተበትነዋል፡ ወጣቶችን እያሳደዱና እያፈሱ መሆኑ፡ የባጃጅ አሽከርካሪዎችን በሰልፉ እንዳይገኙ ብሎም ቅስቀሳ እንዳያደርጉ ዛቻን የተላበሰ ማስጠንቀቂያ እየሰጡ መሆኑ ታውቋል። በአፈሳው በርካታ ወጣቶች ለዕርስ የተዳረጉ መሆኑ የታወቀ ሲሆን፡ ከነዚህም ውስጥ በመንገድ ላይ ንግድ የተሰማሩና ኑሮዋቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ወጣቶች አብላጫውን ቁጥር ይይዛሉ እንደ ዘጋቢያችን ገለፃ። የባጃጅ አሽከርካሪዎች አንድነት ፓርቲ በሚሊዮኖች ድምፅ ለነፃነት ህዝባዊ ንቅናቄ በባህርዳር ባደረገው የተቃውሞ ሰልፍ ላይ በራሳቸው ተነሳሽነት በስፋት የቅስቀሳ ስራ ሲሰሩ እንደነበር የሚታወስ ነው።

## ከሳውዲ ተመላሽ ኢትዮጵያውያን ስቃይ አሁንም እንደቀጠለ ነው

የወያኔው የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተባለው ተቋም ያስጠናው ጥናት ይፋ እንዳደረገው ተመላሾቹ የአዕምሮ ችግር፤ ዘገምተኝነት፤ ሱስ፤ ራስን መጣል፤ የስነ ልቦና ችግር፤ ድብርት ፤ ከሰው መገለል፤ ተስፋ መቁረጥ፤ እራስን ማጥፋት፤ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግሮች፤ አሰገድዶ መደፈር ችግር የጣለባቸው ጠባሳ በህይወታቸው ላይ ከባድ ተጽኖ እንደፈጠረባቸው፡ በከፋ ስቃይ ውስጥ እንደሚገኙ አጋልጧል። በሺዎች የሚቆጠሩ ተመላሺ ኢትዩጵያውያን የኢትዩጵያን መሬት በረገጡ በሳልስቱ በሱዳን ገዳሪፍ በኩል በህገ ወጥ መጉረፍ መጀመራቸው በተደጋጋሚ ተነገረዋል። በመተማ እየሱስ የሃገር ውስጥ ድህነትን ፈርተው በመሸሺ ወደ ሱዳን እና አረብ ሃገራት የሚሰደዱት ቁጥር በቀን 1ሺ 800 የሚገመት መሆኑ የተነገረ ሲሆን ራሳቸውን ስተው በእብደት ደረጃ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች እንዳሉም ተጋልጧል። እንዲሁም ባዶ እጃችንን አንመለስም በማለት በሴተኛ አዳሪነት የድንበር ከተማዋን ከበው በቀን በ10 ብር እና 20 ብር ገንዘብ የሴተኛ አዳሪ ህይዎትን የሚገፉ፡ በሱዳናዊያን ዜጎች እየተደፈሩ የሚኖሩ በርካቶች መሆናቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ። 3 ከስደተኝነት የተመለሱ ኢትዩጵያውያን በተስፋ መቁረጥ ሃገር ቤት በገቡ በቀናት ጊዜ ውስጥ እራሳቸውን ማጥፋታቸው ታውቋል።

## ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ያመረታቸዉ አውቶቡሶች በየመንገዱ መገተራቸዉ ተሰማ

የኢትዮጵያን ህዝብ ለመዝረፍና የወያኔን ባሰስልጣኖች ኪስ ለመሙላት ተብሎ ምንም ሳይታሰብበት በችኮላ በከፍተኛ ወጪ የተቋቋመዉ የኢትዮጵያ የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሺን የሚያመርታቸዉ አዉቶቡሶች በየቦታዉ እየቆሙ አገሪቱ ሸክም መሆናቸዉን ከወደ አዲስ አበባ የሚደርሱን ዜናዎች ያስረዳሉ። የአዲስ አበባን የትራንስፖርት ችግርን ይቀርፋሉ ተብለዉ የተመረቱት እነዚህ አዉቶቡሶች ተገጣጥመው ወደስራ ከተሰማሩ በኋላ በብልሽትና በመለዋወጫ ዕቃ አለመኖር የተነሳ በየቦታው በመቆማቸውየአዲስአበባ ከተማ የትራንስፖርት እጥረት እንዲባባስ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ተሰምቷል።

ከአዲስአበባ መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ የተገኘ መረጃ እንዳመለከተው በአሁኑ ወቅት በኮርፖሬሽኑ ከተገጣጠሙ 500 ገደማ የከተማ አውቶቡሶች ከ110 በላይ የሚሆኑት በብልሽት ምክንያት ከመስመር ውጪ ሲሆኑ የተቀሩትም በትንንሽ የቴክኒክ ችግሮች በየመንገዱ የሚቆሙ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ከተማዋ የትራንስፖርት እጥረት እንዲባባስ አንድ ምክነያት ሆኗዋል።አውቶቡሶቹ በአገር ውስጥ ሲገጣጠሙ ታሳቢ ተደርጎ ነበረው በብልሽት ወቅት የመለዋወጫ አቅርቦት በቅርብ ማግኘት ያስችላል በሚል እንደነበር ነገር ግን አምራቹ የብረታብረት ኮርፖሬሽን የመለዋወጫ ክምችት መያዝ ባለመቻሉ ተሽከርካሪዎቹ በቀላል ብልሽት ጭምር ሊቆሙ እንደተገደዱ ታውቆአል።ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው የቢሮው ሠራተኞች እንደተናገሩት ይህ የመለዋወጫ አንገብጋቢ ችግር ሳይፈታና የቆሙ ተሽከርካሪዎች ማንሳት ሳይቻል ተጨማሪ ከ50 በላይ አውቶቡሶችን ኮርፖሬሽኑ እንዲገጣጥም መታዘዙ በአገር ሐብት ላይ መቀለድ ነው ሲሉ ተቃውሞአቸውን ገልጸዋል። አውቶቡሶቹ ቴክኒካዊ አቋማቸው ደካማ በመሆኑ ለአንበሳ አውቶቡስ ግልጋሎት ለማዋል አስቸጋሪ መሆኑን በተግባር መታየቱን የትራንስፖርት ቢሮው አንዳንድ ሰራተኞች ተናግረው በዚህ ጉዳይ ላይ ገንቢ አስተያየት መስጠት በራሱ በፖለቲካ የሚያስፈርጅና ልማትን እንደማደናቀፍ እያስቆጠረ በመሆኑ ብዙሃኑ ባለሙያ ጭምር ዝምታን መርጦአል ሲሉ አስረድተዋል።

ከሁለት ሳምንት በፊት የትምህርት ሚኒስቴር ሠራተኞችን በመያዝ ወደአማራ ክልል ለስብሰባ ሲጉዋዝ የነበረ በኮርፖሬሽኑ የተገጣጠመ አውቶቡስ አባይ በረሃ ላይ በመገልበጥ በርካታ ሰዎች ለሞት መዳረጉን መነገሩ ይታወሳል።

## የፋሽስት ወያኔ ከጅቡቲ መቀሌ ባቡር ሃዲድ ግንባታ

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

በሆነ የኑሮ ውድነትና አመታዊ አጠቃለይ ምርት እጥረት የተፈጠረው ችግር ያስነሳውን ከፍተኛ የሕዝብ ተቃውሞ ለማፈን የአገልግሎት ኢንዳስትሪዎችን ወደ ክልሉ በማስገባት የክልሉ ሕዝብ በተቀጣሪነት እንኳ በማገልገል ራሱን መደጎም እንዲችል በማድረግ ተቃውሞን ለማፈን ሲሞክር እንደነበር ጠቅሰው የባቡር ሃዲድ መስመሩንም በዚያ በኩል ማድረጉ ከዚሁ ጋር የተያያዘ ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል።

ወያኔ ሕወሃት ከዚህ በፊት የክልሉን ማህበረሰብ ተቃውሞ ለማጥፋት የምርት ግብአታቸውን መቶ በመቶ ከሌሎች ክልሎች የሚያስገቡ ቁጥራቸው ብዙ የሆኑ የማምረቻና የአገልግሎት ተቋማትን በመገንባት እዚህ ግባ በማይባል ወርሃዊ ክፍያ የክልሉን ሕዝብ በማታለል እየገዛው እንደሆነ በተደጋጋሚ መዘገቡ አይዘነጋም።

## 77ኛው የሰማዕታት ቀን

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

የካቲት 12፣ 1929 ዓም የአገራቸዉ የኢትዮጵያ በጠላት እጅ መዉደቅ ያስመረራቸዉ ጀግኖቹ አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም የተባሉ ኢትዮጵያውያን ግራዚያኒን ለመግደል የጣሉትን ቦንብ ተከትሎ፣ የጣሊያን ወራሪ ሰራዊት በወሰደው እርምጃ በሦስት ቀን ዉስጥ ከ30 ሺ በላይ ኢትዮጵያውን መገደላቸው ይታወቃል። በዚህች የአዲስ አበባ አደባባዮች በአገር ልጆች ደም በታጠቡበት ቀን አረመኔዉ ግራዚያኒ በየቦታዉ የሰማራቸዉ ቅጥረኛ ነብሰ ገዳዮች ኢትዮጵያዉያንን ሰቅለዋል፤ አንገታታቸዉን ቀልተዋል፤ በእሳት አቃጥለዋል እብዲሁም ሰዎችን ሰብስበዉ በቡልዶዘር ድጠዋቸዋል። አሳዛኝ ቀን በኢጣሊያን ፋሽስቶች የጦር መሪ ጄኔራል ሮዶልፎ ግራዚያኒ ትዕዛዝ፣ በሶስት ቀናት ውስጥ ብቻ ከ፴ሺህ የማያንሱ ንፁሃን ኢትዮጵያውያን የተጨፈጨፉበት ድርጊት የተጀመረበት ነበር። እንዲያውም በአዲስ አበባ ከተማ እና በአካባቢው ብቻ ሣይሆን በደብረሊባኖስ እና በዝቋላ ገዳማት፣ በፍቼ፣ በደብረብርሃን፣ በደብረማርቆስ እና በሌሎችም የኢትዮጵያ ከተሞች፣ በተለይ የተማሩት እና በአርበኝነት ትግል ይሣተፋሉ ተብለው የሚጠረጠሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እየተለቀሙ የተፈጁት በግራዚያኒ ላይ በቦንብ የግድያ ሙከራ ከመደረጉ በፊት ነበር። ስለዚህ የየካቲት ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. ጭፍጨፋ ሆን ተብሎና ታቅዶ በፋሽስት ጣሊያኖች ታቅዶ የተከናወነ የዘር ማጥፋት ወንጀል መሆኑን መካድ አይቻልም። ኢትዮጵያ ከ፭ ሚሊዮን የማያንሱ ዜጎቿን ገብራ፣ ከ፭ ዓመታት የአርበኝነት ትግል በኋላ ጀግኖች አርበኞቿ በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. የፋሽስት ኢጣሊያንን ድል በማድረግ ነፃነቷን አቀዳጇት። የድሉ መገኘት ለኢትዮጵያውያን አርበኞች ውለታ ተከፋይ ባያደርጋቸውም፣ ለሠማዕታቱ መታሠቢያ የሚሆኑ ሐውልቶችን ግን ለማስገንባት ምክንያት ሆኗል። በዚህም መሠረት በአዲስ አበባ ከተማ።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፐሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## የኢትዮጵያዊዉ ፓይለት የሃይለመድህን አበራ ጉዳይ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

እንዲጽፉም ያስቻለ ጀግና በማለት ድጋፋቸውን እየሰጡት ይገኛሉ። በአየር መንገዱ ውስጥ አለ ስለተባለው ዘረኝነትና ጭቆና ለማጣራት ባደረግነው ሙከራ አንድ ስሙ እንዳይገለጽ የፈለገ በአየር መንገዱ ተቀጥሮ የሚሰራ ሰራተኛ፡ ዘረኝነትና ጭቆና በስፋት መኖሩን በማጋለጥ በዚህም ችግር የተነሳ በርካቶች ስራቸው እየለቀቁ እንደሚገኙ በመግለፅ፡ ሃይለመድህንም በኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ ስላለው ቢሮክራሲና ዘረኝነት ደጋግሞ ይናገርና እጅግም ይማረር እንደነበር ለሬዲዮ ክፍላችን ካደረሰን መልዕክት ለመረዳት ችለናል።

ሃይለመድህን አበራ ላይ እየተሰጡ ካሉ አስተያየቶች ነገር ግን በበርካቶች ዘንድ ጥርጣሬን ያጫረው ድርጊቱን ከጤንነቱ ጋር በማያያዝይ በእህቱ ትንሳኤ አበራ ተጽፏል ተብሎ የተሰራጨው ጽሁፍ ሲሆን፡ ይህም ጥርጣሬ የጉጅሌው ወያኔ የደህንነት ሃይሎች በአለም ደረጃ የተሰማው የረዳት አብራሪው የፖለቲካ ጥገኝነት ጥያቄ ጉዳይ በሃገር ውስጥ ያለውን የስርአቱን ብልሹነት እና ጭቆና ለአለም ይፋ የሚያደርገው በመሆኑ ይህንን ለማስተባበል በሚል እህቱን በማስገደድ እንድትፅፍ ተደርጋ ቢሆንስ የሚለው የበርካቶች ጥያቄ ሆኗል። አንድን ከፍተኛ የአውሮፕላን አብራሪን " ህመምተኛ ነበር" ማለት ማንንም አያሳምንም ሲሉ፡ ከጭንቅላቱ ጀምሮ የታመመው አገዛዙ ነው በማለት ትችታቸውን ይሰነዝራሉ። የኔሰው ገብሬ "ፍትህና ዲሞክራሲ በሌለበት ሀገር መኖር አልፈልግም" ብሎ ራሱን ሲያጠፋ ሹመኞች እህቱን በሀይል በማስገደድ :-"ወንድሜን ያመው ነበር" እንድትል ማስደረጋቸው በማስረጃነት ይጠቅሳሉ። ጋዜጠኛና አክቲቪስት አበበ ገላው ሚቹን መለስ ዜናዊ በተቃውሞ ማስደንገጡን ተከትሎ አልተሳካም እንጂ ካድሬዎች ስሙን ጥላሸት ለመቀባት ብዙ መድከማቸው የማይዘነጋ ሲሆን፡ በተመሳሳይም ዛሬ በሀይለመድህን አበራ ላይ እየተደረገ ያለው የስም ማጥፋትም ከዚህ የዘለለ አይሆንም ሲሉ እምነታቸውን በስፋት እየገለጹ ይገኛሉ። በአገር ቤትና በዉጭ የሚገኙ አያሌ ኦትዮጵያዉአን ካፒቴን ኃይለመድህን ፍላጎቱ የወያኔን ብልሹ ስርዐት ለዓለም ማሳየት እንጂ ጥገኝነት ማግኘት አለመሆኑን በግልጽ በመናገር ላይ ባሉበት በአሁኑ ወቅት ዋሺንግተን ዲሲን ጨምሮ በብዙ የአለም ከተሞች ውስጥ ኢትዮጵያዉያን ወደ ስዊዘርላንድ ኤምባሲ በመሄድ የሲዊዘርላንድ መንግስት የፓይለቱን እዉነተኛ ታሪክ እንዲረዳና ፓይለት ሀይለመድህን አበራን እንደ ፖለቲካ ስደተኛ እንጂ እንደ አዉሮፕላን ጠላፊ አድርጎ እንዳይመለከት ለመጠየቅ በዝግጅት ላይ ናቸዉ። በየከተማዉ የሚገኙትን የሰልፍ አስተባባሪዎች ጠይቀን ባገኘነዉ መረጃ መሰረት የኢትዮጵያዉያን ፍላጎት ፓይለት ሀይለመድህን አበራ የሚያስገፈልጊዉ እርዳታና የወያኔን አገዛዝ አይን የማያይበት ኢጋጣሚ እንጂ አንደ ተራ አዉሮፕላን ጠላፊ ታይቶ ሊቀጣ እንደማይገባዉ ለአለም ህዝብ በተለይም ለሲዊዘርላንድ መንግስት ማሳሳብ ነዉ።

ዛሬ ይሄ ቆራጥ ወጣት በአምባገነኑ ወያኔ ላይ ያላውን እምቢተኝነት ለማሳየት አውሮፕላን መጥለፉን ሲያሻቸው ከውንብድና ሲያሻቸው ደሞ ከአዕምሮ ህመም ጋር ሊያይዙት የሚሞክሩት የጉጅሌው ካድሬዎች አምና እና ካቻምና በንጉሱ ዘመን አውሮፕላን ሊጠልፉ ሲሞክሩ የተገደሉትን ዋላልኝ መኮንን እና አምስት ግብረ አበሮቹን የጠለፉ ታሪክ ለአርባ አመት ሲያሞካሹ መኖራቸውን ማን ይዘነጋዋል በማለት አስተያየታቸውን የሚሰጡም በርካቶቹ መሆናቸውን ዘጋቢያችን የተለያዩ የሶሻል ሚዲያዎችን በማጣቀስ አድርሶናል። በተያያዘ ዜና ሃይለመድህን ባለፈው ጥር ወር ላይ ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች የአጎቱ መገደልን ተከትሎ ከፍተኛ የደህንነት ስጋት ውስጥ እንደነበርም ለማረጋገጥ ተችሏል። አጎቱ ዶ/ር እምሩ ስዩም ባለፈው ጥር ወር ከስራ ሲወጡ ታክሲ ውስጥ ሞተው የተገኙ ሲሆን፣ እስካሁን ድረስ ዶ/ሩን ማን እንደገደላቸው በውል ባይታወቅም፣ አንዳንድ ወገኖች ግን ግድያው ከፖለቲካ ጋር የተያያዘ መሆኑን ይመሰክራሉ። ሃይለመድህን ከአጎቱ ሞት በሁዋላ እርሱም በተመሳሳይ አደጋ ውስጥ እገኛለሁ ብሎ ሲሰጋ እንደነበር፣ በተለይም በአየር መንገዱ ውስጥ የተሰባሰቡት ካድሬዎች፣ ያሳድዱኛል ብሎ እንደሚያስብ ለማወቅም ተችሏል ። ኢትዮጵያዊው ፓይለት ሃይለመድህን አበራ በህዝባችን ላይ የሚፈጸመው ግፍና መከራ እጅግ የሚያንገበግበው ትሁትና ብሩህ አእምሮ የነበረው አብራሪ መሆኑን በቅርብ የሚያውቁት ጓደኞቹ ምስክርነታቸውን እየሰጡ ሲሆን ዝርዝር ጉዳዩን በተመለከተም በመጭው ሰኞ ለስዊዘርላንድ ፖሊስ በስፋት ቃሉን ይሰጣል ተብሎም ይጠበቃል።

## የአንበሳውን ዋሻ

የአንበሳውን ዋሻ ዝንጀሮ ሸንቶበት
ቦታ ማደሪያውን ሁሉን አበላሽቶት
ግማቱ ክርፋቱ አላስቀምጥ ብሎት
እየወጣ ሄደ እየለቀቀለት
ዝንጀሮ ዘለለ ለእሱ ቀን ወጣለት።

የሚባላው ተበይ ሆነ ጊዜ ተቀይሮ
የሚፈራው ፈሪ ሆነ እሳ ዘንድሮ
በአንበሳው ጫንቃ ላይ ዘለለ ዝንጀሮ።

የአንበሳውን ሱሪ ዝንጀሮ ቀዶበት
ጊዜ ጣለውና ደረሰበት ሸንፈት
ግርማና መጎሱ ክብሩ ተነክቶበት
እንዳይቀይር ሌላ ሁሉም ቀዳዳ ሆነበት
ገላውን የሚያሳይ ሁሉን እንደ ወንፊት
ገመናውን አይቶ ዓለምም ሳቀበት
እፍረት ያዘውና ያለቅሳል እንደ ሴት

አለ ተቀምጦ ተከናንቦ ቁጭትና ውርደት።
ሰፍቶ እንዳይታጠቅ ግራ ተጋብቶት
መርፌውና ክሩ ከቤቱ ጠፍተውት
አላውስም አለው ያ ክፉ ጎረቤት
ጊዜ የማይቀየር የማያልፍ መስሎት።
ከዚህ ሁሉ ነገር ከባአዳን ደጅ ከመጥናት
አሮጌውን ጥሎ አዲስ ቢተካበት
ይሻለው ነበረ ከድሪቶ ብዛት
እየደጋገመ መልሶ መላልሶ ከሚጠቀምበት።

ያ ክፉ ጎረቤት ማስተዋል ያቃተው
ሱሪ አይለብስም ነበር እኛ እስከምናውቀው
ጊዜ ሰጠውና አሳምሮ ለብሶ ተሸፈነ ገላው።

አያውቅም ነበረ ሱሪ መታጠቅ
አሁን መልበስ ጀመር እኛ ስናወልቅ
በወገቡ አዞረ ዝናር ሙሉ ትጥቅ።

ቀሚስ ወለቀና ሱሪ ተለበሰ
ሴት እና ወንዱን እያተራመሰ
የአንበሳውን ቦታ ገብቶ አፈራረሰ
ግመል መንዳት ቀርቶ እርሻውን አረሰ
ያልደከመበትን የሰው ምርት አፈሰ
ሱሪ ስለ አስታጠቀው ዜናዊ ለገሰ።

ጊዜ ይረዝማል እንጂ መች ይቀርለታል
የታጠቀውን ሱሪ አውልቆ ይጥላል
አንበሳው ተነስቶ ብድሩን ይመልሳል
ይቅርና ሴቷን ወንዱን አበርክኳል
የሐበሻ ልጅ መች ተገዝቶ ያውቃል
እንኳንስ ለራሱ ለአፍሪቃም አኩርቷል።

ወልቃይት ጠገዴ ኧረ ምኑ ነካህ
የአሳደከው ጥጃ በርግጫ ሲመታህ
ማሰሪያውን ቆርጦ ሲያዞረው በአንገትህ
አንገትክን ብትደፋ እንደ ኤሊ አርጎ አየህ።

እንግዲህስ ይብቃህ ከቤት መዋሉ ማደሩ
ዝምብለህ አትይ አረቦች መሬትክን ሲወሩ
ሁሉም ሰው ይነሳ ዘብ ይቁም ለሀገሩ
ክንድህን አሳይ ለእኚያ ለማይረቡ
አልሰማም ብለዋል ሁሌ ቢነገሩ።

መስከረም፤ ፳ቀን፡ ፪ሺህ /ዓ.ም (30/09/2013)

(በተስፋሁን ሞላ)